# በስመአብ ወወልድ ወመንፈስቅዱስ አሐዱ አምላክ አሜን

## መዝሙር በእንተ ጥምቀቱ ለእግዚእነ ኢየሱስ ክርስቶስ

## ጥራዝ አንድ

54. ሐረ ኢየሱስ
ሐረ ኢየሱስ/4/
እምገሊላ/2/ ኅበ
ዮርዳኖስ
ፈለገዮርዳኖስ/2/
ከመያጥምቆ
ትርጉም፣ ኢየሱስ
ከገሊላ ወደ ዮርዳኖስ
ወረደ በዮርዳኖስ ወንዝ
ለመጠመቅ

55. ወረደ ወልድ
ወረደ ወልድ /6/
እምሰማያት ውስተ
ምጥማቃት/2/
ትርጉም፣ ወልድ
ክርስቶስ ከሰማያት ወደ
ወንዞች ወረደ

56. ውስተ ማኅጸነ
ድንግል
ውስተ ማኅጸነ ድንግል
ኅደረማኅፀነ ድንግል
ሰማይ ወምድር
ዘኢያገምሮ
ሰማይ ወምድር በማይ
ተጠመቀ
ትርጉም፣ ሰማይና
ምድር የማይችሉት
አምላክ በእመቤታችን
ማኅጸን አደረ
በውሃ ተጠመቀ

56. መጽዐ ቃል
መጽዐ ቃል እም ደመና
ዘይብል/2/
ዝንቱ ውእቱ ወልድየ
ዘአፈቅር/4/
መጣ ቃል ከደመና
እንዲህ የሚል/2/
የምወደው የማፈቅረው
ልጄ ይህ ነው/4/

57. የዓለምን በደል
የዓለምን በደል የሰውን
ግፍ አይቶ
ዘጠና ዘጠኙን
መላእክቱን ትቶ
ጽድቅን ለመፈጸም
በደልን አጥፍቶ
የሰላሙ መሪ የሰላሙ
ዳኛ
አምላክ ተወለደ ተጠ
መቀ ለእኛ
የሰማዮች ሰማይ
የማይችለው ንጉሥ
ተወልዶ ሲጠመቅ እኛን
ለመቀደስ
ተራሮች ደንግጠው
ዘለሉ እንደፈረስ
አዝ
ባሕር ተጨነቅች ጠ
በባት መሬቱ
ዮርዳኖስም ሸሸ
አልቆመም ከፊቱ
እንደተናገረው ዳዊት
በትንቢቱ
አዝ
ልጁ በዮርዳኖስ ጽድቅን
ሲመሠርት
መጣ በደመና ሰማያዊው
አባት
እየመሰከረ የልጁን
ጌትነት
አዝ
እንደምናነበው በወንጌል
ተጽፎ
መንፈስ ቅዱስ ታየ
በራሱ ላይ አርፎ
በርግብ ምሳሌ ክንፉን
አሰይፎ
አዝ
ባሕር ስትጨነቅ ተራራ
ሲጨፍር
ሰማዩ ሲከፈት ደመና
ሲናገር
ዓለም በዛሬው ቀን
አየች ይህን ምሥጢር
አዝ

58. አማን በአማን
አማን በአማን አማን
በአማን/2/
መንክር ስብሐተ
ጥምቀቱ/4/
እውነት ነው በእውነት
/4/
ድንቅ ነው የጌታ
ጥምቀት/4/

59. እንዘ ሕፃን
እንዘ ሕፃን ልህቀ
በዮርዳኖስ ተጠምቀ/2/
በዮርዳኖስ /2/
ዮርዳኖስ/2/ተጠምቀ
በዮሐንስ/2/
ትርጉም፣ሕፃን ሆኖ
ጥቂት በጥቂቱ አደገ
በዮርዳኖስ ወንዝ
በዮሐንስ እጅ ተጠመቀ

60. በእደ ዮሐንስ
በእደ ዮሐንስ ተጠምቀ
ኢየሱስ ናዝራዊ/2/
ሰማያዊ/5/ ኢየሱስ
ናዝራዊ /2/
ትርጉም፡ ሰማያዊው
የናዝሬቱ ኢየሱስ
በዮሐንስ እጅ ተጠመቀ

61. ተጠምቀ ሰማያዊ
ሃሌ ሃሌ ሃሌ ሉያ ሃሌ
ሃሌ ሉያ ሃሌ ሉያ/2/
ተጠምቀ ሰማያዊ በዕደ
መሬታዊ/4/
ሃሌ ሃሌ ሃሌ ሉያ ሃሌ
ሃሌ ሉያ ሃሌ ሉያ/2/
አምላክ ሆይ ሕዝቦችህ
ዳኑ በልደትህ
አምላክ ሆይ ሕዝቦችህ
ዳኑ በጥምቀትህ

## ጥራዝ ሁለት

**85. ኢየሱስ ሐረ**
ኢየሱስ ሐረ ሀገረ
□ሴጹ/2/
ዮሐንስ አጥመቆ
በማጹ/2/

ትርጉም፡- ኢየሱስ ወደ
□ሴጹ ሀዊረ ቄ□
ዮሐንስም በው□
አጠመቀው::

**86. መትኃኒነ**
መትኃኒነ ተጠምቀ ነዋ/2/
ጁእዜኒ ለሰላም ንትለዋ/2/

ትርጉም፡- መትኃኒታችን
አነሆ ተጠመቀ አሁንስ
እንግዲህስ ሰላምን
እንከተላት

**87. ጁእዜኒ**
ጁእዜኒ ለሰላም ንትለዋ
ለሰላም/2/
እስመ ተ□ምቀ □ም/2/
መትኃኔዓለም/2/

ትርጉም፡- መትኃኔዓለም
ዛሬ ተጠምቋልና አነሆ
ሰላምን እንከተላት::

**88. መ□ወ ቃል**
መ□ወ ቃል እምደመና
□ጹብል/2/
□□□አ □እማጹ ተርኅ□
ሰማጹ/2/
ትርጉም፡- ቃል ከደመና
መጣ:: ከው□□ም

□ንደሚወጣ ሰማይ
ተከፈተ::

**89. አስተርአየ**
አስተርአየ ገሀደ /2/
በለቢሰ ሥጋ ኮነ ዘመደ
/2/
ትርጉም፡- በ□ልዓ □□፡
ሥጋችንን በመልበስ
ዘመድ ሆነን::

**90. ነአምን**
**/ማ. ቅዱሳን - ቁ.5/**

ነአምን /2/ ክርስቶስሃ
ነአምን መድኅነ /2/
ዘዮሐንስ አጥመቆ
በዮርዳኖስ
ዘዮሐንስ አጥመቆ /2/
በዮርዳኖስ /2/
ናምናለን /2/ መድኅን
ክርስቶስን /2/
ናምናለን ክርስቶስን
ዮሐንስ ያጠመቀውን
በዮርዳኖስ
ዮሐንስ ያጠመቀውን
በዮርዳኖስ ያጠመቀውን
/2/

# ጥራዝ ሦስት

**32. በፍስሐ ወበሰላም**
በፍስሐ ወበሰላም /፪/
ወረደ ወልድ /፪/
ውስተ ምጥማቃት /፪/

ትርጉም፡ በደስታና በሰላም
እግዚአብሔር ወልድ ወደ
መጠመቂያ ወረደ

**33. በፍስሐ ወበሰላም እምሰማያት**
በአስሐ □በሰላም
እምሰማያት /፪/
□ረ□ □ልት □ስተ
ምጥማቃት /፬/

ትርጉም፡-በደስታና በሰላም
እግዚአብሔር ወልድ ወደ
መጠመቂያ ወረደ

**34. ሥጋ ሰብእ መዋቴ**
*ሥጋ ሰብእ መዋቴ /፬/*
ወገብረ መንጦላዕተ /፫/

ትርጉም፡ □ሚሞተውን
የሰውን ሥጋ መሠ□ሪጸ□
አደረገ (ተዋሐደ)

*35.* **አስተርአየ ገሀደ**
አስተርአየ ገሀደ አስተርዓየ
እንዘ ህፃን /፪/
እንዘ ህፃን ልህቀ/፪/
በዮርዳኖስ ተጠምቀ እንዘ
ሕፃን /፪/

ትርጉም፡ በግልጥ ታየ እንደ
ህፃናት ቀስ በቀስ አደገ
በዮርዳኖስ ተጠመቀ::

**36. አንሶሰወ**
አንሶሰወ /፪/ ወአስተርአየ /፪/
በዮርዳኖስ ኧኸ ተጠምቀ
በዮሐንስ /፬/

ትርጉም፡- ተመላለሰ በ□ልዓ
□□ በ□ርዳኖስ ወንዝ
በዩሐንስ □□ ተ□መቀ::

**37. ነድ ለማየ ባሕር**
*/ሰ.ት/ቤ.ት.ማ.መ.ቁ.2/*
ነድ ለማየ ባሕር ከበቦ /፪/
ማየ ባሕር ኀበ የሐውር
ፀበቦ /፬/

ትርጉም፡- እሳት የባሕሩን
ውሃ ከበበው ባሕሩም
የሚሄድበት ጨነቀው::

**38. ክርስቶስ ተወልደ**
*/ወለደነ/*
ክርስቶስ ተወልደ እሰይ
ክርስቶስ ተጠምቀ በማይ
ወለደነ ዳግመ እማይ /፪/
ዳግመ /፪/ ወለደነ ዳግመ
እማይ

ትርጉም፡- ክርስቶስ
ተወለደ፣ ክርስቶስ ተጠመቀ
ዳግም ከውሃ ወለደን

**39. ክርስቶስ ተወልደ**
*/አስተርእዮቱ/*
ክርስቶስ ተወልደ ወተጠ
ምቀ /፪/
አስተርእዮቱ አማን
አስተርእዮቱ /፪/

ትርጉም፡- ክርስቶስ ተወለደ
ተጠመቀ መገለጡም
እውነት ነው::

**40. ግነዩ ለእግዚአብሔር**
ግነዩ ለእግዚአብሔር እስመ
ኄር /፪/
እስመ ለዓለም ምሕረቱ
እስመ ለዓለም /፬/
እናመስግንሽ የአምላክ
እናት በዝማሬ /፪/
የዓለም ቤዛ ነውና
የማኅፀንሽ ፍሬ /፬/
ከሰማየ ሰማያት ወርዶ
ከአንቺ ተወልዶ /፪/
መለኮት ወረደ ዮርዳኖስ
እኛን ለመቀደስ /፬/
በዮሐንስ እጅ ተጠመቀ
ዕዳችንን ፋቀ /፪/
በቸርነቱ አወቀን ከበደል
አራቀን /፬/
በድንግልና የወለድሽው
የአንቺ □ንስ /፪/
የድኩማኖች ብርታት ነው
የሕሙማን ፈውስ /፬/
ስምሽን የጠራ ዝክርሽንም
ያዘከረ /፪/
በመንግሥተ ሰማይ ይኖራል
እንደተከበረ /፬/
ብርሃነ መለኮት ያደረብሽ
አዳራሽ /፪/
ቅድስተ ቅዱሳን ማርያም
ድንግል አንቺ ነሽ /፬/
እመቤታችን እናታችን
ማርያም /፪/
የተማ□ነሽ ይኖራል
ለዘለዓለም /፬/

ድንግልናሽም ሳይለወጥ
ወልድን የወለድሽ
ንጽህተ ንጹሃን ማርያም
አንቺው ነሽ

**41. ኀዲኅ ተስዓ**
ኀዲኅ ተስዓ ወተስዓተ ነገደ
/፪/
ማዕከለ ባህር /፪/ ቆመ
ማዕከለ ባህር /፪/

ትርጉም፡-ዘጠና ዘጠኙን
ነገደ መላእክት ትቶ በባሕር
መካከል ቆመ

**42. አጥመቆ በማይ**
አጥመቆ በማይ /፯/
ዮሐንስ /፫/ አጥመቆ በማይ

ትርጉም፡- ዮሐንስ
መድ□ኂታችንን በውሃ አጠ
መቀው

**43. መጽአ ቃል**
መጽአ ቃል /፪/ እም ደመና
ዘይብል /፪/
እምደመና ዘይብል /፫/
ዝንቱ ወልድየ /፪/

ትርጉም፡- ዘጠና ዘጠኙን
ነገደ መላእክት ትቶ በባሕር
መካከል ቆመ

**44. ዮሐንስኒ ይቤ**
ዮሐንስኒ /፪/ ይቤ ዘአጥመቆ
በዮርዳኖስ /፪/
ርኢክዎ ወስእንኩ ጠይቆቱ
ስእንኩ /፪/

ትርጉም፡ ትርጉም ፡-
በዮርዳኖስ ጌታን ያጠመቀው
ዮሃንስ □ታዬን አየሁት
እርሱን መርምሬ ልደርስበት
አልቻልኩም አስ፡፡

**45. ይእዜኒ ለሰላም**
ጾእዜኒ ለሰላም ንተለዋ
ለሰላም /፪/
ተጠምቀ ነዋ መድ□ኔ ዓለም
መት□ኒነ መት□ኔ ዓለም /፪/

# ጥራዝ አራት

## *38. ዮሐንስኒ ሀሎ*

***/ዘማሪት ማርታ ኃ/ሥላሴ ቁ.፪/***

ዮሐንስኒ ሀሎ
ያጠምቅ/፪/ በሂኖን
ያጠምቅ በሂኖን
አዝ...
መንግሥተ ሰማያት
ቀርባለች እያለ
ዮሐንስ ሲያሰተምር
ማነው ያስተዋለ
እንደ ተናገረ አዋጅ
ነጋሪው
ተራራው ዝቅ ይበል
ይሙላ ጎድጓዳው
አዝ...
እድገቱ ምናኔ ትምህርቱ ንስሐ
የጣዝማ ማር በልቶ ኖረ በበረሃ
መጓዝ እንዲያስችለን
በሕይወት ጎዳና
ላይ ታቺ፤ ይደልደል
ጎባጣውም ይቅና
አዝ...
ሲኖር በምናኔ በሂኖን በረሃ
ያጠምቅ ነበረ ዮሐንስ በውሃ
በማየ ዮርዳኖስ በዮሐንስ እጅ
ጌታ ተጠመቀ ድኅነትን ሊያውጅ
አዝ...
ጌታውን አጥምቆ
ለክብር የሚበቃ
ከእናቱ ማኅፀን ተገኘ
ምርጥ ዕቃ
ኤልሳቤጥም ለክብር ሆና
የታደለች
መልካም የነፍስ አባት
መጥምቁን ወለደች
ዮሐንስኒ ሃሎ
ያጠምቅ/፪/ በሂኖን/፫/

## *39. በዮርዳኖስ ተጠምቀ*

በዮርዳኖስ ተጠምቀ /፪/
በሠላሳ ክረምት /፪/
ከመ ይስዓር መርገማ
ለሔዋን ዲበ /፪/ ዕፀ
መስቀል ተሰቅለ/፪/

***ትርጉም፡- በሠላሳ ዘመኑ***
***በዮርዳኖስ ተጠመቀ***
***ሔዋንንም መርገም***
***ይደመስስ ዘንድ በመስቀል***
***ላይ ተሰቀለ፡፡***

## *40. ርዕዩከ ማያት*

***/ማኅበረ ቅዱሳን ቁ ፮/***

ርዕዩከ ማያት እ□□አ
ርዕዩከ ማያት ወፈርሁ/፪/
ደንገጹ ቀላያተ ማያት
□□ም□ ማጸቲሆሙ
/፬/ኧኸ
አቤቱ ውኆች አዩህ
ውኆችም አይተው
□ሩህ/፪/
ጥልቆችም ተነዋወጡ
ውኆችም ጮኹ/፬/ኧጩ

## *41. ልደቶ ትምቀቶ*

ልደቶ ጥምቀቶ
አስተርእዮቶ ለመድኃኒነ
/፪/
እለ ቀደሙነ/፫/መሃሩ
እለ ቀደሙነ/፪/

***ትርጉም፡-የቀደሙ***
***አባቶቻችን የጌታችንን***
***ልደቱን፣ጥምቀቱን***
***መታየቱን/መገለጡን/***
***አስተማሩን፡፡***

## *42. ወቅድሳተ መንፈስ*

***/ማኅበረ ቅዱሳን ቁ ፮/***

ወቅድሳተ መንፈስ
ወሀበነ ማየ መንጽሔ
ዚአነ
ቅድስት ትዕዛዙን
አፍርሰን
□□ ምትረ ኛጁት
ብንወርድ
በኀጢአት ወጥመድ
ተይዘን በሲኦል እሳት
ስንነድ
የምንዱባንን ጩኸት
ከሰማይ ሆኖ ሰማና
በ□ሙ እንዲቤዥር
ዓለሙን አንድያ ልጁን
ላከና
አዝ...
የሐሰት አባት ሳጥናኤል
የፍጥኝ አስሮን በዕዳ
በዕብነ ሩካብ ጽፎብን
የሞት ደብዳቤ የፍዳ
ነጻ □ንዲያወጣን
በጥምቀት ከሲኦል ኑሮ
ጎዳና
አበሳችንን ሊያስወግድ
ወደ ዮርዳኖስ መጣና
አዝ...
□□□· ተቱ□ □ስ□· ል□
ሲኖር በምውት ገዳም
የጽድቅ ጎዳና ጠፍቶበት
ሲናፍቅ ያችን ዓለም
በአምስተኛው ቀን
ከመንፈቅ ብርሃን
ከምስራቅ ፈንጥቆ
አስወገደለት መርገሙን
ከዮርዳኖስ ወንዝ ተጠምቆ
አዝ...
አብ ከላይ ሆኖ አሰማ
የምስራች ቃል ለሁሉ
□ክ□ □ብ□ቤ ስረ□
ተደርጓልና በሙሉ
ቀለም አበሳ ተፋቀ ዳግም
ተሰጠን ልጅነት
ሕፃኑ ኢየሱስ ክርስቶስ
ከላይ ውሃ ደፍቶበት
አዝ...

## *43. ተጠምቀ ሰማያዊ*

**/ደ/መ/መድኃኔ ዓለም እና**
**ማኅደረ ስብሐት ልደታ**
**ለማርያም ቤ/ክ ተክለ**
**ሳዊሮስ ሰ/ት/ቤት ቁ.፭/**

ተጠምቀ ሰማያዊ/፪/
በእደ መፈጸሚ/፪/
የአምላኮች አምላክ
የነገሥታት ንጉሥ/፪/
የዓለም ሁሉ ፈጣሪ
የሥጋና የነፍስ
አዝ...
ከባርነት አውጥቶ
ነጻነትን ሊሰጠን/፪/
ሐዘናችን አጥፍቶ
ሰላምን ሊመግበን
አዝ...
ጠላታችን አፈረ
አምላካችን ከበረ/፪/
ስለ ልጁ መጠመቅ
እግዚአብሔር መሰከረ
አዝ...
በአንድነት እናቅርብ
ለአምላክ ምስጋና/፪/
እልል እልል እንበል ነጻ
ወጥተናልና
አዝ...
ጥቂት በጥቂት አደገ
በዮርዳኖስ ተጠመቀ/፪/
በዮርዳኖስ /4/ ተጠመቀ
በቅዱስ ዮሐንስ/፪/

## *44. በበህቀ ልህቀ*

በበህቀ ልህቀ /፪/
በሠላሳ ክረምት
በዮርዳኖስ ተጠምቀ /፪/
ጥቂት በጥቂት አደገ /፪/
በሠላሳ ዘመን በዮርዳኖስ
ተጠመቀ /፪/